# ከእሳት አደጋ በኋላ

የእሳት አደጋ ደህንነት የሁሉም ሰው ስጋት ነው። የእሳት አደጋ ከተከሰተ በኋላ ህይወት በድንገት ይቀየራል። በቤትዎ ውስጥ ከተከሰተው የእሳት አደጋ ማገገም ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ አካላዊ እና አእምሮ ፈታኝ ሂደት ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ በጣም አስቸጋሪው ነገር መውሰድ ያለብዎትን እርምጃዎች እና ማንን ማነጋገር እንዳለብዎት ማወቅ ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የእሳት እና ከአደጋ የማዳን አገልግሎት እርስዎ ከአደጋ ለማገገም ለሚያደርጉት ጥረት እንዲረዳዎ ከፌዴራል የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ኤጀንሲ እና ከዩናይትድ ስቴትስ የእሳት አደጋ አስተዳደር የህትመት መረጃዎችን በመውሰድ ይህን መረጃ አጠናክሯል። አብዛኞቹ ምክረ ሃሳቦች አፋጣኝ እርምጃ የሚፈልጉ ሲሆን የተወሰኑት ወደፊት ሊያስፈልጉ ይችላሉ እና ሌሎችም በቀጣይነት የሚያስፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህ መረጃ ህይወትዎን እንደገና መገንባት ሲጀምሩ እንዲያግዝዎ የተዘጋጀ ነው። ስሜት(emotional) ላይ ከሚደርስ ጉዳት ማገገም ቤትን እንደገና እንደመገንባት እና የአካል ጉዳቶችን እንደ ማከም ሁሉ አስፈላጊ ነገር ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የእሳት እና ከአደጋ የማዳን አገልግሎት ህይወትዎን ወደ መደበኛ ሁኔታ በመመለስ ሂደት ውስጥ እርስዎን ለመርዳት የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ለተጨማሪ መረጃ እና አገልግሎቶች እባክዎን ድህረ-ገጻችንን ይጎብኙ። www.mcfrs.org

ከሰላምታ ጋር፣

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የእሳት አደጋ ኃላፊ

### የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንትን ሚና መረዳት

የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት እሳትን ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ ምላሽ ይሰጣል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ቤትን ሰብሮ መግባት በቤቱ ላይ ጉዳት ቢያስከትልም እሳቱን በፍጥነት ለማጥፋት እዲቻል ይረዳል። ትንንሽ እሳቶች እንኳን ከፍተኛ መጠን ያለው ሙቀትና ጭስ ያመነጫሉ ይህም የእሳት አደጋ ተከላካዮች ጭሱን እስኪያገኙ ድረስ እና ሙቀቱን እስኪያስወጡ ድረስ በህንጻዎ ውስጥ የእሳቱን መነሻ ማግኘት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንቱ እሳቱ መጥፋቱን ለማረጋገጥ እና ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል መሰረታዊ የጽዳት እና ውሃ የማስወገድ ስራን ያከናውናል። የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት ከሚወስደው ጊዜያዊ እርምጃዎች ባሻገር ሕንፃውን እና በውስጡ ያለውን ንብረት የበለጠ ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑትን ተጨማሪ እርምጃዎች መውሰድ የባለቤቱ ሃላፊነት ነው።

# <u>የመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት</u>

## የአካል ጉዳት በሚደርስበት ወቅት

በእሳቱ ምክንያት እርስዎ፣ ጓደኛዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል ጉዳት ከደረሰባችሁ እና ጉዳቱ አፋጣኝ የመጀመሪያ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ የተወሰኑ ሂደቶችን መከተል አለብዎት። በስራዎ በኩል የጤና ኢንሹራንስ ፖሊሲ ካልዎት አሰሪዎን ያነጋግሩ ወይም የግል የኢንሹራንስ ካልዎ የኢንሹራንስ ወኪልዎን ያነጋግሩ። የተወሰኑት የቤት ባለቤት ፓኬጅ ፖሊሲዎች በንብረትዎ ወስጥ ለተጎዱ እና የቅርብ ቤተሰብዎ አባላት ላልሆኑ ሰዎች የተወሰነ የህክምና ኢንሹራንስ ይሰጣሉ። የቤት ባለቤት ኢንሹራንስ ፖሊሲ በእሳቱ ምክንያት በርስዎ ላይ ለሚቀርቡት ማንኛውም የሊያቢሊቲ (liability) የተጠያቂነት ክስን በተመለከተ ሽፋን ሊሰጥዎ ይችላል። ለበለጠ መረጃ ወኪልዎን ያነጋግሩ።

## <u>የኢንሹራንስ መረጃ</u>

## ኢንሹራንስ <u>ካልዎት</u>

ኢንሹራንስ ካልዎት፣ ኢንሹራንስዎ ከእሳት አደጋ በኃላ ለማገገም ብቸኛው እና በጣም አስፈላጊው ነገር ይሆናል። የኢንሹራንስ አጀስተር (adjuster) አፋጣኝ ጥገና እንዲያደርጉ ሊረዳዎ ወይም የቤትዎን ደህንነት ለመጠበቅ ሊረዳዎት ይችላል። የኢንሹራንስ ወኪልዎን ማነጋገር ካልቻሉ እና ወደ ቤትዎ ለመግባት የባለሙያ እርዳታ ከፈለጉ አጠቃላይ ኮንትራክተርን ወይም የእሳት አደጋ መልሶ ማቋቋም ድርጅትን ማነጋገር ይችላሉ። ለማንኛውም የመልሶ ማስተካከል አገልግሎት ለማግኘት ከመዋዋልዎ <u>በፊት</u> ከኢንሹራንስ አጀስተርዎ (insurance adjuster) ጋር መነጋገር በጣም አስፈላጊ ነው። ያለ እነሱ እውቅና ወይም ፍቃድ በመዋዋል የኢንሹራንስ ድርጅቱን ሃላፊነት ሊጥሱ ይችላሉ።

በመኖሪያ ቤትዎ በአፋጣኝ መሰራት ያለባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለቦት የኢንሹራንስ ድርጅትዎን ይጠይቁ፣ ይህም በሮች፣ መስኮቶች እና ሌሎች ክፍት የሆኑ ቦታዎችን መሸፈን እና ውሃን ማስወገድን ያካትታል።

ከእርስዎ የሚፈለጉትን እርምጃዎች በተመለከተ የኢንሹራንስ ድርጅትዎን ያማክሩ። አንዳንድ የመመሪያዎች ባለቤቶች (policy holders) የተበላሹ የግል ንብረቶችን ብዛት፣ አይነታቸውን እና ለእቃዎቹ ምን ያህል እንደከፈሉ በዝርዝር የሚያሳይ ዝርዝር እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

የተከራዮች ወይም የንብረት ኢንሹራንስ ይኑርዎት። ተከራዮች ጋር ያለው የተለመደ የተሳሳተ ግንዛቤ ኢንሹራንስ በአከራያቸው በኩል ያላቸው ይመስላቸዋል። ምንም እንኳን አከራዮች የኢንሹራንስ ፖሊሲ ቢኖራቸውም፣ ይህ ለመኖሪያ ሕንፃው ጉዳት ብቻ ዋስትና የሚሰጥ ነው። የእነርሱ የኢንሹራንስ ፖሊሲ በእርስዎ በአፓርታማ ውስጥ ያሉ የግል ንብረቶችን አይሸፍንም። ለቤት ባለቤቶች፣ ተከራዮች ወይም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባለቤቶች በርካታ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች አሉ። ብዙ አማራጮችን እንዲመረምሩ እና ለእርስዎ ተስማሚ የሆነ ፖሊሲ እንዲመርጡ በጥብቅ ይመከራል።

የእርስዎ የኢንሹራንስ ፖሊሲ በእርስዎ እና በኢንሹራንስ ሰጪው መካከል ያለ ውል ነው። ከእሳት አደጋ በኋላ የእርስዎ ኃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- **አደጋው ስላስከተለው ኪሳራ ለኢንሹራንስ ድርጅቱ ወይም ለኢንሹራንስ ሰጪው ወኪል ወይም አገናኝ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለብዎት።**
- በጣራ ላይ ወይም በግድግዳ ላይ ያሉትን ቀዳዳዎች በመሸፈን አስፈላጊ ጥገናዎችን በማድረግ ንብረትን ከተጨማሪ ጉዳት መጠበቅ።
- ቤቱን ለተወሰነ ጊዜ የማያሞቁት ከሆነ በዊንተር ወራት የውሃ መስመሮችን መክፈት እና ማፍሰስን የመሳሰሉ ከኪሳራ የሚታደጉ ተመጣጣኝ ጥንቃቄዎችን ማድረግ። የኢንሹራንስ ድርጅቱ እንደዚህ ያሉ ምክንያታዊ ጥንቃቄዎች ባለመደረጋቸው ምክኒያት የሚከሰቱ ኪሳራዎች ላለመክፈል አቋም ሊይዙ ይችላሉ።
- ብዛት፣ የእቃው አይነት መግለጫ፣ መጀመሪያ የተገዛበት ዋጋ፣ የግዢ ቀን፣ የጉዳት ግምት እና የሚተካበትን የወጪ ግምት በማካተት የተበላሹ/የተጎዱ የግል ንብረቶችን ዝርዝር ማዘጋጀት። **ለኢንሹራንስ የሚያቀርቡትን ጥያቄዎን የሚደግፉ ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲችሉ ጉዳቱን የደረሰበትን ስፍራ ፎቶግራፎች ማንሳትን ወይም ቪዲዮ መቅረጽን ግምት ውስጥ ያስገቡ።**
- የተበላሹ ንብረቶችን ለኢንሹራንስ ድረጅቱ ወይም አጀስተሩ (adjuster) በማቅረብ መተባበር።
- **ለኢንሹራንስ አጀስተር ወይም ለኢንሹራንስ ድርጅቱ የሰጡትን ሁሉንም ሰነዶች እና የፎቶ ቅጂዎች ለራስዎ ቀሪ ፋይል መያዝ ይኖርብዎታል።**

እንዲሁም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ **አደጋው ያስከተለውን ኪሳራ የሚያሳይ የጽሁፍ ማስረጃ** ማስገባት ይኖርብዎታል። እንደዚህ ያሉ መግለጫዎች በአብዛኛው ጊዜ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ንብረቱ የወደመበት ጊዜ እና መንስኤው።
- በንብረቱ ላይ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች ስም እና አድራሻ። እነዚህም የቤቱን ሞርጌጅ የሰጠው አካል፣ የተለያዩ ወይም የተፋቱ የትዳር ጓደኛ ወይም የተመዘገበ የቤቱ ባለቤትን ሊያካትት ይችላል።

- የሕንፃው ፕላን እና የመጀመሪያው ቤት ዝርዝሮች እና ለጥገናዎች ዝርዝር ግምት።

## የእሳት ጉዳት ግምገማ

የሞንጎመሪ ካውንቲ የእሳት እና ከአደጋ የማዳን አገልግሎት ዲፓርትመንት ቤትዎ በእሳት አደጋ ምክንያት ጉዳት ከደረሰበት ለቤቶች ዲፓርትመንት ያሳውቃል። የፍተሻ እና የፈቃዶች ዲፓርትመንት የእሳት ቃጠሎውን መጠን እና ለመጠገን ምን አይነት ፈቃዶች እንደሚያስፈልግ ለማወቅ የቤትዎን ፍተሻ ያካሂዳል። ማንኛውንም ጥገና ከማድረግዎ በፊት እባክዎን የፈቃድ እና የፍተሻ ዲፓርትመንትን ያነጋግሩ እና ይህ የተከሰተው በእሳት አደጋ መሆኑን በማሳወቅ ፈቃዶች በፍጥነት እንዲሰጡ ያድርጉ። ሁልጊዜ ማንኛውንም ጥገና ከኢንሹራንስ ድርጅቶ ጋር አስቀድመው በማሳወቅ ተግባራዊ ያድርጉ።

## ቤተሰብዎን መልሶ ማቋቋም

ቤትዎ ለመኖሪያ የማይመች ከሆነ እና ማደሪያ ማግኘት ካልቻሉ፣ ለምሳሌ ከቤተሰብ ወይም ከጓደኞችዎ ጋር፣ ተጨማሪ የኑሮ ወጪዎች ኢንሹራንስዎ እንደሚሸፍን ለማወቅ የእርስዎን የኢንሹራንስ ካምፓኒ ያማክሩ። ጊዜያዊ የማደሪያ ቦታ ለመከራየት እስኪያመቻቹ ድረስ ቀይ መስቀል ጊዜያዊ መጠለያ ሊሰጥ ይችል ይሆናል።

## የመልሶ ማቋቋም አገልግሎቶች

እርስዎ ወይም የእርስዎ ኢንሹራንስ የእሳት አደጋ መልሶ ማቋቋም ድርጅት አገልግሎት ሊቀጥሩ ይችላሉ። **ለማንኛውም አገልግሎት ከመዋዋል በፊት ከኢንሹራንስ ኩባንያ/አጀስተር ጋር በጋራ መስራት አስፈላጊ ነው። ያለ እነሱ እውቅና ወይም ፍቃድ ለአገልግሎቶች ውል በመግባት የኢንሹራንስ ድርጅቱን ኃላፊነት ከጣሱ ፣ በኢንሹራንስ ሰጪው ሊሸፈን የሚችለውን ክፍያ እርስዎ እንዲከፍሉ ሊገደዱ ይችላሉ።**

ማንኛውንም ድርጅት ለጥገና ከመቅጠርዎ በፊት አስፈላጊውን ማጣሪያ ያድርጉ። እነዚህ ድርጅቶች ከሚከተሉት ውስጥ የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም ሊያካትቱ የሚችሉ ሰፊ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡-

- መኖሪያው ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ መጠበቅ።
- የህንጻውን መዋቅራዊ ጉዳቶችን መገመት።
- የህንጻውን መዋቅራዊ ጉዳቶችን መጠገን።
- የግል ንብረቶችን ለመጠገን ወይም ለማደስ የሚወጣውን ወጪ መገመት።
- የቤት እቃዎችን ማሸግ፣ ማጓጓዝ እና ስቶር ውስጥ ማስቀመጥ።
- ተገቢውን የጽዳት ወይም ተጨማሪ ኮንትራክተሮችን መከታተል ።

  አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ የተጠገኑ ዕቃዎችን ስቶር ማድረግ።

## ንብረትዎን ይጠብቁ

የኢንሹራንስ ፖሊሲዎ እንዲቀጥል ቀሪውን የግል ንብረትዎን ለመጠበቅ "አስፈላጊውን እንክብካቤ" ማድረግ አለብዎት። የተበላሹ መስኮቶችን እና በሮች ያሽጉ እና በጣራው ላይ ያሉትን ቀዳዳዎች በፕላይውድ (plywood)፣ ታርፕስ (tarps)፣ እና ታር ፔፐር (tar paper) ይሸፍኑ።። የአየር ሁኔታው ቀዝቃዛ ከሆነ፣ ሁሉም የቧንቧ መስመሮች መዘጋታቸውን እና ሁሉም ውኃ ፈሶ ማለቁን ያረጋግጡ። እንደ ማብሰያ ምድጃ ፣ ሙቅ ውሃ ማሞቂያ እና የእሳት መሞቂያ ያሉ መሳሪያዎች ደህንነታቸው እንዲረጋገጥ የጋዝ ካምፓኒውን ያነጋግሩ። በድጋሚ ከማገናኘትዎ በፊት ሁሉም የተጎዱ የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች እና ሽቦዎች ደህንነታቸው እና አገልግሎታቸው እንዲረጋገጥ ብቃት ያላቸውን የኤሌትሪክ ባለሙያ ያነጋግሩ። የእሳት አደጋ ተከላካዮች ቆጣሪዎን ቢያነሱ ወይም አገልግሎትዎን ከቆረጡ የኤሌክትሪክ ኩባንያውን ያነጋግሩ ወይም የኤሌክትሪክ ባለሙያዎ እንዲጠግነው ያድርጉ። ሁሉንም አገልግሎቶች ከኢንሹራንስ ኩባንያዎ/አጀስተርዎ ጋር አስቀድመው ማሳወቅዎትን ያረጋግጡ። ከእነዚህ አገልግሎቶች እንዲከፍሉ ከተደረጉ፣ ደረሰኞችዎን ከእሳት አደጋው ጋር በተያያዘ ለወጣው ወጪ ማረጋገጫ ስለሚሆን ያስቀምጡ። ይህ በእርስዎ የገቢ ታክስ ላይ የሚያስገቡትን የእሳት አደጋው ኪሳራዎችን ለማረጋገጥ ይረዳል።

## ኢንሹራንስ <u>ከሌለዎት</u>

ንብረትዎ ኢንሹራንስ ከሌለው ወይም ኢንሹራንስዎ ሁሉንም ኪሳራዎን የማይሸፍን ከሆነ መመሪያ ለማግኘት የቤተሰብ ጠበቃዎን ወይም የሀገር ወስጥ ገቢ አገልግሎትን (አይአርኤስ) ያነጋግሩ። በአደጋ ምክኒያት ንብረትን ማጣትን ለተመለከተ ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የሀገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት ቢሮን (አይአርኤስ) ያነጋግሩ እና **:- ህትመቶች 547 ስለ አደጋዎች፣ የአደጋ ኪሳራ እና ስርቆቶች የታክስ መረጃን ይጠይቁ።**

ኢንሹራንስ ከሌለዎት እና እርዳታ ከፈለጉ፣ እርዳታ ለማግኘት የአካባቢዎን የአደጋ ጊዜ እርዳታ አገልግሎቶችን ያነጋግሩ። የአሜሪካ ቀይ መስቀል በማንኛውም ቀን በሳምንት ሰባት ቀን ሊረዳዎ ዝግጁ ነው። እንዲሁም እንደ ምግብ፣ አልባሳት እና መኖሪያ ቤት ላሉ አስቸኳይ ፍላጎቶችዎ ሊረዱዎት ይችላሉ ብሎም በማህበረሰብዎ ወስጥ ሊረዱዎት የሚችሉ ኤጀንሲዎችን በመለየት ሊያግዝዎት ይችላሉ።

የእርዳታ ወይም የመረጃ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ የግል ድርጅቶች፡-

- የአሜሪካ ቀይ መስቀል
- ሳልቬሽን አርሚ (Salvation Army)
- የሃይማኖት ተቋማት
- የማህበራዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት
- የሲቪክ ድርጅቶች
- የእስቴት ወይም የማዘጋጃ ቤት የድንገተኛ ጊዜ አገልግሎት ቢሮ
- ለትርፍ ያልተቋቋሙ የችግር ወቅት አማካሪ ማዕከሎች

## ጠቃሚ ማስጠንቀቂያዎች፡-

- **በአደጋው ምክኒያት ወደ ወደመው ቦታ አይግቡ።** የመኖሪያ ቦታዎ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ከእሳት አደጋ ዲፓርትመንት ያረጋግጡ። የአካባቢው ባለስልጣናት ይህን ማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ብለው እስከ አላሳወቅዎት ድረስ በእሳቱ የተጎዱ ቦታዎችን ለማመልከት በበሮች ወይም በመስኮቶች ላይ የተቀመጠውን ባለ ቀለም ቴፕ አልፈው እንዳይገቡ። ያስታውሱ፣ እሳቶች ሳይታዩ የተቃጠሉ ካሉ ነገሮች እንደገና ሊቀጣጠሉ ይችላሉ ።

- የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት የፍጆታ መገልገያዎች (ውሃ፣ ኤሌትሪክ እና የተፈጥሮ ጋዝ) ከቤቱ ከመውጣታቸው በፊት ለአጠቃቀም ምቹ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። የተዘጉ የፍጆታ መገልገያዎችን እራስዎ ለመክፈት አይሞክሩ።

- በእሳቱ ምክንያት ለሚከሰተው የሕንጻው መዋቅራዊ ጉዳት አደጋ እንዳያስከትል ተጠንቀቁ። ጣሪያዎች እና ወለሎች ሊበላሹ እና ሊወድቁ ይችላሉ።

- ለሙቀት፣ ለጢስ፣ ለጥቀርሻ እና ለውሃ የተጋለጡ ምግቦችን፣ መጠጦችን እና መድሃኒቶችን መጠቀም የለብዎትም።

## ከቤትዎ መልቀቅ፡-

ቦታው ሰው የማይኖርበት መሆኑን ለማሳወቅ የአካባቢዎን የፖሊስ ዲፓርትመንትን ያነጋግሩ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሰዎች ወደ ቤቱ እንዳይገቡ ለማድረግ ማንኛውንም ክፍት ቦታ ወይም መግቢያ ማሸግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ከአደጋው በኋላ ወዲያውኑ ለሚያወጡት ወጪ ሁሉንም ደረሰኞች ያስቀምጡ። ደረሰኝ ለኢንሹራንስ ድርጅት ከእሳት አደጋው ጋር በተያያዘ ያወጡትን ገንዘብ ለማሳየት እና እንዲሁም በገቢ ታክስ ላይ የሚጠይቁትን ኪሳራዎች ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው።

**ይህን ለማድረግ አደጋ የማያስከትል ከሆነ የሚከተሉትን ነገሮች ለማግኘት ይሞክሩ።**

- እንደ መንጃ ፈቃድ እና የማህበራዊ ዋስትና ካርዶች ያሉ ሰነዶችን።
- የኢንሹራንስ መረጃ።
- የመድሃኒት መረጃ።
- የዓይን መነፅር፣ የመስሚያ መርጃዎች (hearing aids) ወይም ሌሎች የሰው ሰራሽ የአካል መሳሪያዎች።
- እንደ ክሬዲት ካርዶች፣ የባንክ ደብተሮች፣ ጥሬ ገንዘብ እና ጌጣጌጥ ያሉ ዋጋ ያላቸው ነገሮች።

ወደ ሌላ ቦታ ስለመዛወርዎ ማወቅ ያለባቸው ብዙ ሰዎች/አካላት አሉ። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የኢንሹራንስ ድርጅቶ
- የሞርጌጅ ድርጅቶ
- ቤተሰብዎ፣ ጓደኞችዎ እና ጎረቤቶችዎ
- አሰሪዎ
- የልጅዎ ትምህርት ቤት
- በአቅራያብያዎ ያለ ፖስታ ቤት
- እና ማንኛውም እቤት ድረስ እቃ የሚያመጡ አገልግሎቶት ሰጪዎች
- የአካባቢዎ የእሳት እና የፖሊስ ዲፓርትመንት
- የፍጆታ (utility) መገልገያ አቅራቢ ድርጅቶች

## በምርመራ ላይ ያሉ የእሳት አደጋዎች

የፋየር ማርሻል ቢሮ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ወይም የኢንሹራንስ ድርጅቶ የእርስዎን የእሳት አደጋ እየመረመሩ ከሆነ ቤትዎ ወይም ተሽከርካሪዎ ወስጥ ያለውን እቃ ከማውጣትዎ፣ ከመቀየርዎ ወይም ከማንቀሳቀስዎ በፊት የተጠቀሱትን ድርጅቶች ያማክሩ።

## ለንብረትዎ ዋጋ መስጠት

**ከእሳት አደጋው በፊት የተሰራ የንብረት ቆጠራ** እና ሁሉንም ንብረትዎ የሚያሳይ የቪዲዮ ካለ ጥያቄዎን(claim) በሚያቀርቡበት ጊዜ ጠቃሚ መረጃ ሊሆን ይችላል።

## ኪሳራውን ማስተካከል

"የኪሳራ ማስተካከያ"/"Loss adjustment" **የወደመውን ንብረት ዋጋ የማውጣት** ሂደት ነው። ይህ በብዙ ወገኖች መካከል የሚተገበር የጋራ ጥረት ውጤት ነው። የሂደቱ መሰረታዊ አካላት የቤቱ ባለቤት ወይም ነዋሪ፣ የኢንሹራንስ ድርጅቱ እና ተወካዮቹ ናቸው።

በተለምዶ ባለቤቱ ወይም ነዋሪው የእቃ ዝርዝር እንዲያዘጋጅ በኢንሹራንስ ድርጅቱ ይጠየቃል እና በኪሳራ ግምገማ ሂደት ውስጥ እንዲተባበር ይጠየቃል። ኪሳራው መጠነኛ ከሆነ የኢንሹራንስ ወኪሉ እንደ አጀስተር (adjuster) በመሆን ሊያገለግል ይችላል። የኢንሹራንስ ድርጅቱ የኢንሹራንስ ድርጅቱ ቋሚ ሰራተኛ የሆነ አጀስተር (adjuster) ሊልክ ይችላል፣ ወይም የኢሹራንስ ድርጅቱ ራሱን ወክሎ የሚሰራ አጀስተር (adjuster) ሊቀጥር ይችላል። የኢንሹራንስ አጀስተር (adjuster) ሥራ የኢንሹራንስ ድርጅቱ ተወካይ ሆኖ የኪሳራ ግምገማ ሂደትን መከታተል እና መርዳት እና ኪሳራውን ወደ ፍትሃዊ እና እኩል የሆነ መፍትሄ ማምጣት ነው።

- ☑ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ሳያልቁ የተበላሹ/የወደሙ እቃዎችን እንዳይጥሉ፡፡ የኢንሹራንስ ጥያቄዎን (claim) ለማጠናከር ሁሉም ጉዳቶች ግምት ውስጥ ይገባሉ።
- ☑ ኢንቬንቶሪ ወይም የጥገና አገልግሎት ለማግኘት ከማሰብዎ በፊት ዕቅዶችዎን ከኢንሹራንስ ወኪልዎ/ድርጅቶ ጋር ይወያዩ።

# <u>የተሽከርካሪ እሳቶች</u>

## ኢንሹራንስ ካለዎ

የኢንሹራንስ ወኪልዎን ያነጋግሩ። ስለ ኢንሹራንስዎ ሊያብራሩሎት እና ስለ ክሌምዎ (claim) ሊረዱዎት ይችላሉ። ተሽከርካሪዎ በመኖሪያ ቤት እሳት ጉዳት ከደረሰበት፣ ሁለቱንም የቤትዎን እና የተሽከርካሪ ኢንሹራንስ ወኪሎችን ያግኙ።

## ኢንሹራንስ ከሌልዎት

ተሽከርካሪው ሊጠገን የሚችል ከሆነ፣ የጥገና ቦታዎች ዝርዝር በየሎው ፔጅ ውስጥ "የአውቶሞቢል ጥገና እና አገልግሎት" “Automobile Repair and Service.” በሚለው ስር ውስጥ ይገኛል።

ቶው (tow) ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ በየሎው ፔጅ ውስጥ “የአውቶሞቢል የመንገድ ላይ አገልግሎት” “Automobile Repair and Service.” በሚለው ስር ይመልከቱ ወይም ፖሊሲዎ ቶው ማድረግን የሚሸፍን ከሆነ ወይም የተለየ መስፈርት ካሎት የኢንሹራንስ ወኪልዎን ያማክሩ።

ተሽከርካሪው ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰብት፣ አሮጌ መኪና የሚከማችበት ቦታ (salvage yard) በኩል ዋጋ ሊኖረው ይችላል። የተጎዱ ተሽከርካሪዎች ማከማቻ ቦታዎችን ዝርዝር በየሎው ፔጅ ውስጥ "አውቶሞቢል ማከማቻ" “Automobile Salvage.” በሚለው ስር ይገኛል።

## ተሽከርካሪዎች  በተመለከተ የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት ስራዎች እና የስራ የሂደቶች

አልፎ አልፎ፣ የእሳት አደጋ ተከላካዮች ተሽከርካሪውን በመስበር ወደ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ይህ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የእሳት አደጋ አለመኖሩን ማረጋገጥ እና ማንኛውንም እሳት ለማጥፋት ያግዛል።  እሳቱ ሙሉ በሙሉ መጥፋቱን ለማረጋገጥ የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት የሚከተሉትን ሊያደርግ ይችላል፦

1. በኤሌክትሪክ ገመዶች ምክኒያት እሳት እንዳይፈጠር ለመከላከል የባትሪ ኬብሎችን መቁረጥ እና/ወይም ማላቀቅ።

2. በመቀመጫዎች ላይ ያሉ በተለይም በጥጥ የተሰራ መቀመጫ ካለ ማውጣት።

3. እሳቱን ለማጥፋት ወደ ተሳፋሪ መቀመጫ ስፍራ ፣ የተሽከርካሪው የሞተር እና እቃ መጫኛው ክፍል ውስጥ መግባት፣ የኤሌክትሪክ ገመዱን ይፈትሹ እና የባትሪ ገመዶችን ቦታቸው ላይ መኖራቸውን ያረጋግጡ።

## <u>የቤት እንስሳት</u>

ጭስ የውሻ ወይም የድመት ሳንባን በደቂቃዎች ውስጥ ይጎዳል እና  የእሳት ፍንጣቂ በቤት እንስሳዎ ፀጉር ስር ተደብቆ በመቆየት ከባድ ህመም ያለው ቃጠሎ ያስከትላል። ውሾች ይጮሀሉ እና እሳቱ ከተነሳበት ቦታ ራቅ ብለው ይሮጣሉ እና ብዙ ጊዜ የእሳት አደጋ መኪናዎች ድምጽ ያስፈራቸዋል። ድመቶች ከቤት እቃዎች ስር እና ወደ ጓዳ ውስጥ በመግባት ከእሳት መደበቅ ይፈልጋሉ እና በተለምዶ ከውሾች የበለጠ በጭስ ለመታፈን ተጋላጭ ናቸው።

የፈራ እንስሳ ሊናከስ ወይም ሊቧጭር ይችላል። የቤት እንስሳትን በጥንቃቄ እና በእርጋታ ይያዙ። የእሳት አደጋ ውስጥ የነበረ ማንኛውም እንስሳ ብዙውን ጊዜ በጢስ እና በጥቀርሻ ይሸፈናል። ድመቶች እራሳቸውን በመላስ ያጸዳሉ እናም የጭስ ሽታ እስከሚጠፋ ድረስ እራሳቸውን ይልሳሉ። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ በጣም ጎጂ ሊሆኑ የሚችሉትን ጥቀርሻ እና ሌሎች እሳቱ ያስከተላቸውን ነገሮች ወደ ውስጣቸው ያስገባሉ። የእሳት አደጋ ውስጥ የነበሩ ድመቶች በጥንቃቄ እና በደንብ ለብ ባለ ውሃ እና በሕፃናት ሻምፑ መታጠብ አለባቸው ። ይህንን እራስዎ ሊያደርጉት ይችላሉ ነገር ግን ብዙ የቤት እንስሳት ባለቤቶች ይህ ብቃት ባለው የእንስሳት ሐኪም ወይም የእንስሳት ሕክምና ሰራተኛ በሆነ ግለሰብ ሲከናወን በእንስሳው ላይ ዝቅተኛ ጫና እንደሚኖረው ይገልጻሉ።

☑ የቤት እንስሳዎን መለየት እንዲቻል የእርስዎን የመገኛ አድራሻ የያዘ ታግ እንዳላቸው እርግጠኛ ይሁኑ። የቤት እንስሳዎ ግራ በመጋባት ከጠፉ፣ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የእንስሳት ቁጥጥር ቢሮዎች ይደውሉ።

***ከእሳት አደጋ በኋላ በተቻለ ፍጥነት የቤት እንስሳዎን (ዎች) ለምርመራ ወደ እንስሳት ሐኪምዎ እንዲወስዱ ይመከራል።***

# የኢንሹራንስ ውሎችን መረዳት

በኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቃሚው በትክክል የማይረዳቸው የተለመዱ ቃላት አሉ። የእሳት አደጋ ኪሳራን ለማስተካከል ወይም በፌደራል ታክስ ላይ የአደጋ ኪሳራ ለመጠየቅ በንብረትዎ ዋጋ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ያጋጥሞታል። የሚከተሉትን ቃላት ማወቅ የእሳት አደጋ ኪሳራ ዋጋን ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋለውን የአሰራር ሂደት ለመረዳት ይረዳዎታል።

ለንብረቶቻችሁን በሁለት መንገድ ኢንሹራንስ መግባት ይችላሉ፦ በጥሬ ገንዘብ ዋጋ ወይም በምትክ ዋጋ። የትኛው ኢንሹራንስ እርስዎ ላሉበት ሁኔታ የተሻለ እንደሆነ ከወኪልዎ ወይም ከኢንሹራንስ ድርጅቶ ተወካይ ጋር በመሆን መገምገምዎን ያረጋግጡ።

በእሳት አደጋ ምክኒያት በግል እቃዎችዎ ላይ የደረሰውን ኪሳራ ለመለካት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፣ እነዚህ እቃዎች ለእርስዎ የተለየ እና በገንዘብ የማይለካ ዋጋ አላቸው። ነገር ግን፣ እርስዎ፣ ኢንሹራንስዎ እና የሀገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት( IRS) የሚጠቀሙባቸው ደረጃቸውን የጠበቁ መለኪያዎች ለሚያደርጉት ውይይት እንደመነሻ ሆነው ያገለግላሉ።

## በተገዙበት ጊዜ የነበራቸው ዋጋ

ይህ የእቃውን የመጨረሻ ዋጋ ለመወሰን አስፈላጊ ነገር ነው። ደረሰኞች እቃው የተገዛበትን ዋጋ/የሚያወጣውን ዋጋ ለማረጋገጥ ይረዳሉ።

## ከእሳት አደጋው በፊት የነበረ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

ይህ ጽንሰ-ሀሳብ እንደ ትክክለኛ የገንዘብ ዋጋ (ACTUAL CASH VALUE)ተደረጎ ይወሰዳል። ይህ ከእሳት አደጋው አንድ ቀን በፊት ቢሸጡት ከእቃው ሊያገኙ የሚችሉት የዋጋ መጠን ነው። ዋጋው የሚሰላው ከተገዛበት ዋጋ ላይ የአገልግሎት ጊዜው በመቀነስ ነው።

## ትክክለኛው የገንዘብ ዋጋ (Actual Cash Value)

ይህ እርስዎ እንደ ኢንሹራንስ ባለቤት የወደመውን ንብረት ከአደጋው ጊዜ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ እንዲቻል የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን ነው። የመጠገን ሂደቱ ሲጠናቀቅ፣ የንብረትዎ ዋጋ መጨመር የለበትም። ትክክለኛው የጥሬ ገንዘብ ዋጋ (ACV) ሲቀበሉ በኪሳራዎ ምክንያት ከትክክለኛው ዋጋ በላይ ማግኘት የለብዎትም። ትክክለኛው የጥሬ ገንዘብ ዋጋ (ACV) የሚወሰነው በአደጋው ጊዜ የአዲስ እቃዎች ዋጋ፣ እንዲሁም የጉልበት እና ሌሎች ክፍያዎችን ጨምሮ ፣ የንብረቱ የአገልግሎት ጊዜ (መቆሸሽ፣ መፋፋቅ፣ የቅርስነት ዋጋ) ተቀንሶ ሲሆን ይህም ከአደጋው በፊት የነበረውን የእቃውን ዋጋ ለማግኘት ያስችላል።

## የእርጅና ቅናሽ (Depreciation)

እቃ ሲያገለግል ዋጋው ይቀንሳል ማለት አንድ እቃ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካገለገለ በኃላ የሚያጣውን ዋጋ ለመግለጽ የሚያገለግል መደበኛ ቃል ነው።

## የመተኪያ ዋጋ (Replacement Cost)

የንብረት ውድመት ኢንሹራንስ ሲገዙ "የመተካት ወጭ/replacement cost" አማራጭን ከመረጡ "የመተካት ወጪ" የሚለው ቃል "ትክክለኛውን የጥሬ ገንዘብ ዋጋ" ተግባራዊ እንዳይሆን ያደርጋል እና የአገልግሎት ጊዜ ዋጋ ቅነሳን ግምት ውስጥ ሳያስገባ ሁሉም የንብረት ዋጋ አሮጌውን በአዲስ እቃ መተካትን ግምት ውስጥ ያስገባል።

**<u>ከእሳት አደጋ በኋላ ዋጋ (Value after the Fire)</u>**

ይህ አንዳንድ ጊዜ የእቃው የማያገለግል ከሆነ የሚኖረው ዋጋ ነው።

# <u>የገንዘብ ምትክ (Money Replacement)</u>

**የዩኤስ ቁጠባ ቦንዶችዎ/U.S. Savings Bonds** ከተበላሹ ወይም ከወደሙ፣ የደረሰውን ኪሳራ የሚያረጋግጥ ማመልከቻ ሲያስገቡ ማስያዣው (bond) ያለምንም ወጪ ይተካል። ቦንዶቹ የተሰጡበትን ቀናት እና ሴርያል ቁጥሮች የሚያሳይ መዝገብ ከቦንዶቹ በተለየ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ቢያስቀምጡ ጠቃሚ ይሆናል። በቦንዶቹ ላይ ስም(ዎች) እና አድራሻ(ዎች)፣ የተገዛበት ግምታዊ ቀን ወይም ጊዜ፣ የዶላር መጠናቸውን እና የእያንዳንዳቸውን ግምታዊ ቁጥር ያካቱ። የኪሳራ ዝርዝሮች፣ በከፊል የተቃጠሉ ወይም የተበላሹ ቦንዶች ጨምሮ ወደ ሚከተለው ቢሮ መላክ አለባቸው፡-

> የሕዝብ ዕዳ ቁጠባ ቦንዶች ኦፕሬሽን
> የሕዝብ ዕዳ ዲፓርትመንት ቢሮ (The
> Bureau of the Public Debt
> Department of Public Debt
> Saving Bonds Operations)
> P.O. Box 1328
> Parkersburg, WV 28106-1328

የፒዲኤፍ (PDF) 1048 ቅጽን መሙላት እቃውን በፍጥነት ለመተካት ይረዳል። እነዚህ ቅጾች ብዙ ጊዜ በአካባቢዎ ያሉ ባንኮች ውስጥ ወይም በአቅራቢያው ከሚገኝ የፌዴራል ሪዘርቭ ባንክ (Federal Reserve Bank) ወይም ቅርንጫፍ ወይም ከሕዝብ ዕዳ ቢሮ (Bureau of the Public Debt) ይገኛሉ። ማንኛውም እንደገና የተሰጡ ማስያዣዎች (bonds) መጀመሪያ የተሰጠበትን ቀን ይኖራቸዋል።

የተቃጠለ ገንዘብን በተቻለ መጠን በጥንቃቄ ይያዙ። እያንዳንዱን ዶላር ወይም የዶላሩን የተወሰነ ክፍል በፕላስቲክ መጠቅለያ ውስጥ ለማስቀመጥ ይሞክሩ። ገንዘቡ በግማሽ ወይም ከዛ ባነሰ የተቃጠለ ከሆነ (ግማሹ ወይም ከዚያ በላይ ደህና ከሆነ) በአዲስ ለመተካት  ወደ አካባቢዎ የፌደራል ሪዘርቭ ባንክ መውሰድ ይችላሉ። በአቅራቢያዎ ያለውን የፌደራል ሪዘርቭ ባንክ ለማወቅ ባንክዎን ይጠይቁ ወይም የተቃጠለውን ወይም የተቀደደውን ገንዘብ በ"በተመዘገበ ፖስታ/registered mail፣ የመመለሻ ደረሰኝ/return receipt " ወደ ቢሮ መላክ ይችላሉ።

የገንዘብ ስታንዳርድ መሥሪያ ቤት
የኢንግሬቪንግ እና የህትመት ቢሮ የግምጃ
ቤት ዲፓርትመንት / Department of
the Treasury Bureau of
Engraving and Printing Office of
Currency Standards
P.O. Box 37048
Washington, DC 20013

የተበላሹ ወይም የቀለጡ ሳንቲሞች ወደ የክልልዎ የፌደራል ሪዘርቭ ባንክ መውሰድ ወይም በ"በተመዘገበ ፖስታ/registered mail ፡የመመለሻ ደረሰኝ/return receipt " ወደ ሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ፡-

ተቆጣጣሪ
የዩኤስኤ ሚንት (U.S. Mint)

P.O. Box 400
Philadelphia, PA 19105

## የታክስ መረጃ

ከእሳት አደጋ በኋላ ውስን የገንዘብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ያሉ ልዩ ድጋፎችን በተመለከተ ከሂሳብ ባለሙያ፣ ከታክስ አማካሪ ወይም ከሀገር ወስጥ ገቢ አገልግሎት (IRS) ያረጋግጡ።

# እቃዎችን ለማስወገድ የሚረዱ መረጃዎች

ብቁ የእሳት እና የውሃ ጉዳት ጥገና ባለሙያ ደረጃውን የጠበቀ የጽዳት እና የግል ንብረቶችን ወደ ነበሩበት ለመመለስ የሚያስችል አገልግሎት ለማግኘት ጥሩ አማራጭ ነው። መመሪያ እና ምክሮችን ለማግኘት ሁል ጊዜ ከኢንሹራንስ ድርጅቶ ጋር ይማከሩ። ሆኖም፣ በሚከተሉት ጠቃሚ ምክሮች አንዳንድ ንብረቶችን ወደ ነበሩበት መመለስ ይችሉ ይሆናል፦

### አልባሳት

ጥንቃቄ ፦ ማንኛውንም አልባሳት ለማጽዳት ከመሞከረዎ በፊት ልብሶቹን ይፈትሹ እና የአምራቹን መመሪያዎች ይከተሉ። በዚህ ቀጥሎ የተገለጹት በርካታ የጽዳት ድብልቆች ትራይ-ሶዲየም ፎስፌት(Tri-Sodium Phosphate) የተባለውን ንጥረ ነገር ይይዛሉ። ይህ ንጥረ ነገር ትራይ-ሶዲየም ፎስፌት(Tri-Sodium Phosphate/TPS) በሚል ስም ሊገዛ ይችላል። ትሪይ-ሶዲየም ፎስፌት (Tri-Sodium Phosphate) በተለምዶ ለጽዳት ጥቅም ላይ የሚውል ንጥረ ነገር ነው እና በጥንቃቄ ጥቅም ላይ መዋል እና ህጻናት እና የቤት እንስሳት በማይደርሱበት ቦታ መቀመጥ አለበት። የጎማ ጓንቶችን ያድርጉ እናም አስፈላጊ መመሪያዎችን ለማወቅ የተለጠፈውን መለያ (label) ያንብቡ።

### መርገጫዎች እና ምንጣፎች

መርገጫዎች እና ምንጣፎች በደንብ እንዲደርቁ መደረግ አለባቸው። ተንቀሳቃሽ ምንጣፎችን አየር ላይ ማውጣት ፣ በቫኩም እና በሻምፑ ማጽዳት ይቻላል። ምንጣፎች በተቻለ ፍጥነት መድረቅ አለባቸው ፦ ዘርግተው ያስቀምጧቸው እና ሙቅ እና ደረቅ አየር የሚያገኙበት ስፍራ ላይ ያድርጉዋቸው። ፋን (fan) መከፈት ምንጣፎቹን ቶሎ ለማድረቅ ይረዳል። ምንጣፎቹ በደንብ መድረቃቸውን ያረጋግጡ። ምንም እንኳን የምንጣፉ የላይኛው ክፍል ደረቅ ቢመስልም የታችኛው ክፍል ስር የሚቀረው እርጥበት ምንጣፉ በፍጥነት እንዲበሰብስ ያደርጋል። ምንጣፎችን ስለማጽዳት እና ስለመጠበቅ መረጃ ለማግኘት ምንጣፍ ሻጭዎ ወይም ብቁ የሆነ የምንጣፍ ጽዳት ባለሙያ ጋር ይደውሉ።

### ቆዳ እና መጽሐፍት

የቆዳ እቃዎችን በደረቅ ጨርቅ ይጥረጉ፣ ከዚያም ጨርቁን ያድርቁ። ቦርሳዎች ቅርጻቸውን ይዘው እንዲቆዩ በጋዜጣ ይጠቅጥቋቸው። ሻንጣዎችን ክፍት አድርገው ያስቀምጡ። የቆዳ ምርቶች ከሙቀት እና ከፀሃይ ርቀው መድረቅ አለባቸው።

የረጠቡ መፃህፍት በተቻለ ፍጥነት እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል። እርጥብ መጽሃፎችን ለማዳን በጣም ጥሩው ዘዴ በቫኩም ፍሪዘር ፍሪዝ ማድረግ ነው። ይህ ልዩ ማቀዝቀዣ ገጾቹን ሳይጎዳ እርጥበቱን ያስወግዳል። እንዲህ ዓይነቱን ማቀዝቀዣ ለማግኘት ካልቻሉ፣ የቫኩም ፍሪዘር እስኪገኝ ድረስ በተለመደው ፍሪዘር ውስጥ ያስቀምጧቸው። በአካባቢዎ ያሉ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያን ማነጋገር ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

### መቆለፊያዎች እና ማጠፊያዎች

መቆለፊያዎች (በተለይም የብረት መቆለፊያዎች) ተፈትተው በዘይት መጠረግ አለባቸው። መቆለፊያዎች ሊነቀሉ ካልቻሉ የማሽን ዘይት በመክፈቻ ቀዳዳው ወይም በቁልፍ ቀዳዳ በኩል በማፍሰስ ዘይቱ እንዲሰራጭ አጀታውን ያነቃንቁት። ማጠፊያዎች በደንብ ማጽዳት እና በዘይት መቀባት አለባቸው።

## ግድግዳዎች፣ ወለሎች እና የቤት እቃዎች

ከግድግዳዎች፣ የቤት እቃዎች እና ወለሎች ላይ ጥቀርሻ እና ጭስ ለማስወገድ መጠነኛ ሽታ ያለው ሳሙና ወይም የልብስ ሳሙና ይጠቀሙ ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መፍትሄዎች በአንድ ላይ ያዋህዱ።

- ከ 4 እስከ 6 የገበታ ማንኪያ (tbsp) ትሪይ-ሶዲየም ፎስፌት (Tri-Sodium Phosphate)
- 1 ኩባያ የቤት ማጽጃ ወይም የክሎሪን ብሊች
- 1 ጋሎን የሞቀ ውሃ

## ያስታዉሱ ፡-

- ሲያጸዱ የጎማ ጓንቶችን ያድርጉ። ግድግዳዎችዎን እና የቤት እቃዎችዎን በንጹህ ሙቅ ውሃ እና በዚህ ኬሚካል ካጠቡ በኋላ በደንብ ማድረቅዎን ያረጋግጡ።
- ከወለሉ በመጀመር ከታች ወደ ላይ በአንድ ጊዜ ትንሽ ትንሽ ቦታን ይጠቡ። ከዚያም ግድግዳውን ወዲያውኑ በንጹህ ውሃ ይጠቡ። ጣሪያዎች መታጠብ ያለባቸው መጨረሻ ነው።
- ግድግዳዎች እና ጣሪያዎች ሙሉ በሙሉ ሳይደርቁ ቀለም መቀባት የለባቸውም።

የግድግዳ ዎልፔፐር (wallpaper) ሊጠገን ይችላል። የተላጠ ጠርዝ ወይም ክፍል እንደገና ለመለጠፍ ፐላስተር ይጠቀሙ። ስለ ዎልፔፐር (wallpaper)ማጽጃዎች መረጃ ለማግኘት የዎልፔፐር (wallpaper)ሻጭዎን ያነጋግሩ። ሊታጠብ የሚችል ዎልፔፐር (wallpaper) እንደ ማንኛውም ግድግዳ ሊጸዳ ይችላል፣ ነገር ግን ወረቀቱን ላለማበስበስ መጠንቀቅ አለብዎት። እንዳይቀደድ ለመከላከል ከታች ወደ ላይ ይጽዱ።

## ከእንጨት የተሰሩ እቃዎች

- ጭቃን ፣ በናኝን እና የተጋገረ ቆሻሻን ያፅዱ ። የቤት ዕቃዎችዎን ፀሐይ ላይ አያደርቁ። እንጨቱ ይላላል እና ቅርጹን ያጣል።
- መሳቢያዎችን ያውጧቸው። መልሰው በሚያስገቡበት ጊዜ ምንም የሚያጣብቅ ነገር እንዳይኖር በደንብ እንዲደርቁ ያድርጉ።
- የእንጨት እቃዎችን ወይም የቤት እቃዎችን በጠንካራ ብሩሽ እና በማጽጃ ኬሚካሎች ያጽዱ።
- እርጥብ እንጨት ሊበሰብስ እና ሊሻግት ይችላል፣ ስለዚህ በደንብ መድረቅ አለበት ። ጥሩ አየር እንዲዘዋወር በሮችን እና መስኮቶችን ይክፈቱ።

- ሻጋታ ከተፈጠረ፣ እንጨቱን ከሙቅ ውሃ ጋር በተዋሀደ የቦርክስ (borax) ውህድ ውስጥ በተነከረ ጨርቅ ይጥረጉ። ነጭ ነጠብጣቦችን ለማስወገድ ግማሽ ኩባያ አሞኒያ (ammonia) እና ግማሽ ኩባያ ውሃ ውስጥ በተነከረ ጨርቅ እንጨቱን ይጥረጉት።  ከዚያም ያድርቁት እና በሰም ይቦርሹ ወይም ግማሽ ኩባያ ተርፔንቲን (turpentine) እና ግማሽ ኩባያ የተልባ ዘይት ውህድ ውስጥ በተነከረ ጨርቅ ይወልውሉት።  ይጠንቀቁ፡- ተርፐንቲን (turpentine) ተቀጣጣይ ነገር ነው።

- እንዲሁም እንጨቱን ጥሩ ጥራት ባለው በፈሳሽ ሰም ውስጥ በተነከረ የሱፍ ጨርቅ ማሸት እና ቦታውን በለስላሳ ጨርቅ እና ከዚያም በንፋስ ማድረቅ እና ማጽዳት ይችላሉ።

## የሚበላሹ (ረጅም ጊዜ የማይቆዩ) ምግቦችስ?

ለሙቀት ወይም ለጭስ የተጋለጡ ማናቸውም ምግቦች፣ መጠጦች እና/ወይም መድሃኒቶች ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም። ምግቦቹ እና እቃዎቹ በጥብቅ በተዘጉ ወይም በታሸጉ ኮንቴይነሮች ውስጥ ከሆኑ ወይም አየር በማይገባበት ፍሪጅ ወይም ፍሪዘር ውስጥ ከነበሩ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።  ደህንነታቸው የተጠበቀ ምግቦችን ስለመመገብ የተለየ መመሪያ እና ምክሮችን ለማግኘት ከአካባቢው የጤና ተወካዮች ጋር ይማከሩ።  ጤንነትዎን አደጋ ላይ ከመጣል እነዚህን ምግቦች ወይም እቃዎችን በአዲስ መተካት ብልህነት ነው።

## ፎቶግራፎች

የተበላሹ ፎቶግራፎችን ወደነበሩበት መመለስ መቻል ብዙ ጊዜ ለእሳት፣ ለጎርፍ እና ለሌሎች አደጋዎች ተጎጂዎች በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።  ጉዳቱ በጣም ከባድ ካልሆነ እራስዎ ወደነበረበት መመለስ ይችላሉ። እያንዳንዱን ፎቶግራፍ በዲጂታል መንገድ ስካን (scan) ማድረግ ይችላሉ። ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ፎቶዎችን ማተም እንዲቻል ፎቶዎቹ እንደ  300dpi ባለ ከፍተኛ ጥራት ባለው ደረጃ ስካን (scan) መደረጋቸውን ያረጋግጡ። ፎቶዎቹን በከፍተኛ ጥራት ስካን ማድረግ ወደነበሩበት መመለስ እንዲቻል ያግዛል፣ ምክንያቱም ፎቶውን ለማስተካከል ቀላል ስለሚሆን ነው።

የወቅቱን ቴክኖሎጂ እና የፎቶ እድሳት ባለሙያዎችን በመጠቀም ፎቶዎች ብዙ ጊዜ ደህንነታቸው ተጠብቆ ሊቆዩ ይችላሉ።  አንድ ላይ የተጣበቁ ፎቶግራፎችን  በመላጥ ለማለያየት በጭራሽ አይሞክሩ።  ፎቶግራፎችን መልሶ ለማደስ ባለሙያ እና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት  የሎው ፔጅ (yellow page) ይመልከቱ።

---

# የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት አሰራር

***<u>ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች፡-</u>***

**ጥያቄ ፡- መስኮቶች ለምን ይሰበራሉ ወይም ጣሪያው ላይ ቀዳዳዎች ይታያሉ?**
እሳት በሚቀጣጠልበት ጊዜ መጀመሪያ ወደ ላይ ከዚያም ወደ ውጭ ይሄዳል። ? መስኮቶችን መስበር እና/ወይም ጣሪያውን መቅደድ (አየር ማናፈሻ ተብሎ የሚጠራው) እሳቱ ወደ እላይ በመውጣት የሚያደርሰውን ጉዳት ይቀንሳል፣ የሚነደውን እሳት የሚሸፍነውን ጭስ ለማስወጣት ይረዳል እና የእሳት አደጋ ተከላካዮቹ እሳቱን በብቃት ማጥፋት እንዲችሉ ያስችላቸዋል።  የዚህ ድርጊት ውጤት በረጅም ጊዜ የሕንጻው መዋቅር ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ዝቅተኛ ነው።

**ጥያቄ፦ ግርግዳዎች ለምን ይፈርሳሉ ወይንም ይቦደሳሉ?**
ይህ የሚደረገው የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንቱ እሳቱ ሙሉ በሙሉ መጥፋቱን እና በግድግዳው ውስጥ ወይም በሌሎች ድብቅ ቦታዎች ውስጥ ምንም እሳት እንደሌለ እርግጠኛ እንዲሆን ነው።

**ጥያቄ፦ የእሳት አደጋ ሪፖርት ኮፒ ማግኘት ይቻላል?**
ከድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የታካሚ ሪፖርቶች ወይም የእሳት አደጋ ሪፖርት መረጃ ለመቀበል ወደ 3-1-1 ወይም 240-777-0311 በመደወል ያነጋግሩ ።

ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ተቀባይነት ያለው ጥያቄ ካቀረቡ በ 30 ቀናት ውስጥ መረጃው ይሰጥዎታል።

# ጠቃሚ ሰነዶችን እና መዝገቦችን መተካት

ከተበላሹ መተካት የሚያስፈልጉዎትን ሰነዶች ዝርዝር እና ስለ አተካኩ ሂደት መረጃ ለማግኘት ማንን ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅ የሚከተለውን ዝርዝር ይመልከቱ።

| የእቃው አይነት | ማንን ማነጋገር አለብዎት |
|---|---|
| የእንስሳት መመዝገቢያ ሰነዶች | ሁሚን ሶሳይቲ (Humane Society) |
| የባንክ ደብተሮች (ቼኪንግ ፣ ሴቪንግ ፣ ወዘተ) | ባንክዎን ፣ በተቻለ ፍጥነት |
| የልደት፣ ሞት እና የጋብቻ የምስክር ወረቀቶች | በስቴትዎ የሚገኙ የመዝገብ ቢሮዎች |
| የዜግነት ሰነድ | የዩኤስ የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት |
| ክሬዲት ካርዶች | የሰጡዎትን ካምፓኒዎች፣ በተቻለ ፍጥነት |
| የፍቺ ሰነድ | ውሳኔ የተሰጠበት የሰርኪውት ፍርድ ቤት |
| የመንጃ ፍቃድ | የሞተር ተሽከርካሪዎች ዲፓርትመንቶች |
| የገቢ ታክስ መዝገቦች | ታክስ ያሰሩበት አይአርኤስ (IRS) ቢሮ ወይም የእርስዎ የሂሳብ ሰራተኛ። |
| የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች | የኢንሹራንስ ወኪልዎ |
| የሕክምና ሪኮርድ | ዶክተርዎ |
| ከወታደራዊ አገልግሎት የስንብት ሰነድ | የቬተራን (Veteran) ጉዳይ ዲፓርትመንት |
| የሞርጌጅ ሰነዶች | የብድር ተቋም |
| ፓስፖርቶች | የፓስፖርት አገልግሎት |
| አክሲዮኖች(stocks) እና ቦንዶች | የሰጠው ካምፓኒ ወይም የእርስዎ ደላላዎ(broker) |
| የማህበራዊ ዋስትና ወይም የሜዲኬር ካርዶች | የአካባቢ የማህበራዊ ዋስትና ( Social Security Office) ቢሮ |
| አክሲዮኖች(stocks) እና ቦንዶች | የእርስዎ ጠበቃ |
| የውርስ ሰነዶች | ንብረቱ የሚገኝበት አካባቢ የሚገኙ የመዝገቦች ዲፓርትመንት |
| ዋስትናዎች | ሰጪ ካምፓኒ |
| ኑዛዜዎች | የእርስዎ ጠበቃ |
| ዋስትናዎች | ሰጪ ካምፓኒ |

# የተከራይ ኢንሹራንስ

## የተከራዮች ኢንሹራንስ ምንድን ነው?

ተከራይተው ለሚኖሩ ሰዎች ፣ የተከራይ ኢንሹራንስ በግል ንብረትዎ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ወይም ኪሳራ ሽፋን ይሰጣል። ከቤት ባለቤት፣ ከንብረት አስተዳዳሪ፣ ወይም ከዩኒቨርሲቲ (በዶርም ውስጥ የሚኖር ተማሪ) ተከራይተው የሚኖሩ ከሆነ የተከራይ ኢንሹራንስ መግዛትን ግምት ውስጥ ያስገቡ።

## ለምን የተከራዮች ኢንሹራንስ መግዛት አስፈለገ?

***የአከራይዎ የኢንሹራንስ ፖሊሲ እርስዎን አይሸፍንም።***

ተከራዮች ጋር ያለው የተለመደ የተሳሳተ ግንዛቤ ኢንሹራንስ በአከራያቸው በኩል ያላቸው ይመስላቸዋል። ምንም እንኳን አከራዮች ኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ቢኖራቸውም፣ ነገር ግን የእነርሱ ኢንሹራንስ የሚሸፍነው እንደ እሳት፣ በረዶ እና የንብረት መውደም ያሉ ክስተቶች ሲፈጠሩ የመኖሪያ ሕንፃው ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ብቻ ነው። በመሆኑም የአከራዩ የኢንሹራንስ ፖሊሲ በአፓርታማዎ <u>ውስጥ ያሉ</u> የግል ንብረቶችን <u>አይሸፍንም</u> ።

ብዙ ሰዎች ስለ ኢንሹራንስ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያስቡት ለመጀመሪያ መኪናቸው ወይም ቤታቸው ኢንሹራንስ መግባት ሲያስቡ ነው። ብዙውን ጊዜ ይህ የሚሆነው ህግ ወይም ባንክ ስለሚጠይቅ ነው። ምንም እንኳን የተከራይ ኢንሹራንስ ብዙ ጊዜ ግዴታ ባይሆንም፣ መኖሩም አስፈላጊ ነው። የግል ዕቃዎችዎን ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ጊዜያዊ የመኖሪያ ቤት ለማገኘት እና የሊያቢሊቲ (liability) ጥበቃ ይሰጥዎታል ለምሳሌ፡- በንብረትዎ ውስጥ ላሉ ሰዎች ያልታሰበ አደጋ ቢገጥማቸው የሕክምናቸውን ወጪ እና ክስ ቢመሰርትብዎ የጠበቃ ወጪ ለመሸፈን ያስችሎታል። አንዴ የተከራይ ኢንሹራንስ ፍላጎትዎን ከወሰኑ በኋላ ያሉዎትን አማራጮች ማወቅ ተሻለ ፖሊሲ ለመምረጥ ይረዳዎታል።

***የተከራዮች ኢንሹራንስ ከአደጋ ይጠብቅዎታል***

የተከራዩት ቤት ጣሪያ በማዕበል፣ በበረዶ ወይም በንፋስ ምክኒያት ከተጎዳ ፣ ጣሪያው በአከራይዎ ኢንሹራንስ ይሸፈናል። ጉዳት ስለ ደረሰባቸው አዲሱ ኮምፒውተርዎ እና ቲቪዎስ? ጣሪያው በሚጠገንበት ጊዜ ፣ ሌላ የመኖሪያ ቦታ ለማግኘት በቂ ገንዘብ አለዎት? የሚከተሉት በእርስዎ የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ የሚሸፈኑ ነገሮች ናቸው። የእርስዎን የግል ንብረት እና የኑሮ ወጪዎች ከመሸፈን በተጨማሪ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎ በሌሎች ወይም በንብረታቸው ላይ ያደረሱትን ኪሳራ ወይም ጉዳት ይሸፍናል።

የተከራይ ኢንሹራንስ ለእርስዎ እንደሚያስፈልግ ከወሰኑ፣ ፖሊሲዎን ሲገዙ በዋጋው እና በሽፋን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አንዳንድ ነገሮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብዎታል።

1. የኢንሹራንስ ሽፋን በዶላር መጠን፡- ይህ በዋጋ እና በኢንሹራንስ ሽፋን ውስጥ ትልቅ አስተዋጾ አለው። ለእያንዳንዱ ንብረት የዶላር መጠን አይወሰንም። ነገር ግን ለአጠቃላይ ንብረትዎ የተወሰነ የገንዘብ መጠን ይወሰናል። እርግጥ ነው፣ ተጨማሪ ኢንሹራንስ ሲገዙ፣ የፖሊሲው ዋጋ ከፍ ያለ ይሆናል።

2. ተቀናሽ (Deductible) :- ይህ ኢንሹራንስዎ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በኢንሹራንስ ክፍያው ላይ እና ምን ያህል ከኪስዎ ለመክፈል ፈቃደኛ እንደሆኑ ለማስላት ያግዛል። ተቀናሽ (deductible) ያለው የኢንሹራንስ ሽፋን ከሊያቢሊቲ (liability) ኢንሹራንስ በስተቀር ለሁሉም ይሰራል።

3. ትክክለኛው የጥሬ ገንዘብ ዋጋ (Actual Cash Value) ወይም የመተኪያ ወጪ (Replacement Cost) ፦ የኢንሹራንስ ድርጅቱ ለኮምፒዩተርዎ እና ለቲቪዎ ምትክ ሊከፍልዎት ሲዘጋጅ፣ ምን ይህል እንደሚሰጡዎት የሚወሰነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው። መደበኛ (basic) የሆነ ፖሊሲ ትክክለኛውን የጥሬ ገንዘብ ዋጋ (ACV) ይከፍልዎታል፣ ይህም ኪሳራው በደረሰበት ጊዜ የነበረው የንብረቱ ዋጋ ነው። ነገር ግን የምትክ ክፍያን ካልመረጡ፣ የእቃውን ትክክለኛ ምትክ ያገኛሉ። ለምሳሌ፣ የ 5 አመት እድሜ ያለው ቲቪ አዲስ ተመሳሳይ ቲቪ ለመግዛት የሚያስችለውን ያህል ገንዘብ ያገኛሉ። ለስርቆት የተጋለጡ እንደ ጌጣጌጥ እና ሸጉጥ ያሉ ውድ እቃዎች ውስን የኢንሹራንስ ሽፋን ስላላቸው እነዚህን እቃዎች በተለየ ፖሊሲ ውስጥ ማካተት ብልህነት ነው። የምትክ ዋጋ (Replacement cost) ከሚያስከፍሎት ተጨማሪ ትንሽ ገንዘብ የበለጠ ጠቀሜታ አለው።

4. አካባቢ እና ቀድመው የቀረቡ ጥያቄዎች (claims)፦ ለስርቆት በተጋለጠ አካባቢ ከተከራዩ ለኢንሹራንስዎ የበለጠ ይከፍላሉ እና እርስዎ ወይም የቀድሞ ነዋሪ ወይም ጎረቤቶች ከዚህ ቀደም ብዙ የኢንሹራንስ ጥያቄዎች (claims) አቅርበው ከሆነ ይህ በእርስዎ ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ ሊያደረግ ይችላል።

ምንም እንኳን የግል ንብረትዎ ለኢንሹራንስ በቂ ዋጋ እንደሌለው ከተሰማዎት፣ የሊያቢሊቲ ኢንሹራንስ ብቻ ያለው የተከራይ ኢንሹራንስ መግባት ጥሩ ነው።

***የተከራይ ኢንሹራንስ መግባት ለወደፊት የቤት ባለቤት ኢንሹራንስ ለመግዛት ይረዳዎታል።***

የተከራዮች ኢንሹራንስ ከኢንሹራንስ ድርጅቶች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖርዎት ያግዝዎታል። ቤት ለመግዛት እያሰቡ ከሆነ፣ የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ መኖሩ የቤት ፖሊሲ ለመግዛት ያለውን ሂደት ቀላል ያደርገዋል በተጨማሪም ቅናሽ ሊያገኙ ይችላሉ።

***የተከራዮች ኢንሹራንስ ስንት ነው?***

በሚገርም ሁኔታ የመሠረታዊ የተከራዮች ኢንሹራንስ ፖሊሲ የዓመት ክፍያ ከ 200 ዶላር ያነሰ ነው። በአስር ወይም በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ዶላር የሚያወጣ የግል ንብረት ያላቸው ወይም ትልቅ የሊያቢሊቲ (liability) ኢንሹራንስ የሚያስፈልጋቸው ተከራዮች የበለጠ ሊከፍሉ ይችላሉ። የኢንሹራንስ ክፍያዎ በበርካታ ሁኔታዎች ላይ ይወሰናል ፦ይህም በቀድሞው የኢንሹራንስ ታሪክዎ እና በሚኖሩበት አካባቢ ሊወሰን ይችላል። እንደ ብሔራዊ የኢንሹራንስ ኮሚሽነሮች ማኅበር፣ በ2000 የተከራይ ኢንሹራንስ በአገር አቀፍ ደረጃ ለዓመታዊ ፖሊሲ 175 ዶላር ነበር፣ ምንም እንኳን ክፍያው ከስቴት ወደ ስቴት የሚለያይ ቢሆንም። የተከራይ ኢንሹራንስ ዝቅተኛ ዋጋ የሚያስከፍል እና ከፍተና ጥቅም ያለው ቢሆንም፣ በ 2003 በገለልተኛ አሜሪካ የኢንሹራንስ ኤጀንሲዎች እና ደላሎች የተደረገ የሕዝብ አስተያየት እንደሚያሳየው በኪራይ ቤቶች ውስጥ ከሚኖሩት ምላሽ ሰጪዎች መካከል 64 በመቶው የተከራይ ኢንሹራንስ አልነበራቸውም።

***ሌላ ምን ማወቅ አለብኝ?***

በተጨማሪም፣ ለእርስዎ የሚስማማውን የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ መምረጥዎን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ያስገቡ። በመጀመሪያ ሁሉም የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ተቀናሽ (deductible) አላቸው። ዝቅተኛ ተቀናሽ (deductible) ሲኖረው የሚከፈለው የኢንሹራንስ መጠን ከፍ ያል ይሆናል። ተቀናሹን (deductible) ከፍ በማድረግ የኢንሹራንስ ክፍያውን ዝቅ ማድረግ ቢችሉም፣ አደጋ ቢከሰት ተቀናሹን (deductible) መክፈል እንደሚችሉ እርግጠኛ ይሁኑ። ሁለተኛ፣ ማወቅ ያለብዎት የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች የማያካትቷቸው ነገሮች አላቸው። መደበኛ (basic) ፖሊሲዎች በአጠቃላይ እንደ ጎርፍ እና የመሬት መንቀጥቀጥ ላሉ የተፈጥሮ አደጋዎች እና ለጠፉ እንደ ጌጣጌጥ ወይም የጥበብ ስራ ላሉ አንዳንድ እቃዎች መጥፋት ዋስትና አይሰጥዎትም። ነገር ግን ፣ ለእነዚህ ኪሳራዎች ዋስትና ለመስጠት የሚያስችል ተጨማሪ ኢንሹራንስ መግባት ይችላሉ።

***የተከራይ ኢንሹራንስ እንዴት መግዛት እችላለሁ?***

የተከራይ ኢንሹራንስ መግዛት ቀላል ነው። የተከራዮች ኢንሹራንስ በኦንላይን መግዛት ይችላሉ ወይም በአካባቢዎ ከሚገኝ የኢንሹራንስ ወኪል መግዛት ይችላሉ። አንዳንድ የኢንሹራንስ አቅራቢዎች የመኪና ኢንሹራንስ ላላቸው ሰዎች ቅናሽ ይሰጣሉ። የእርስዎ የመኪና ኢንሹራንስ እንደዚህ አይነት ቅናሾች እንዳለው ያረጋግጡ።

# ከእሳት አደጋ በኋላ

የሚከተለው ዝርዝር፣ እሳት ከተነሳ በኋላ ወዲያውኑ እንዲጠቀሙበት እንደ ፈጣን ማጣቀሻ እና መመሪያ ሆኖ ያገለግላል።

- ☑ ጊዜያዊ መኖሪያ ቤት፣ ምግብ እና መድሃኒት ከፈለጉ እንደ የአሜሪካ ቀይ መስቀል (American Red Cross) ያሉ የአካባቢዎን የአደጋ እርዳታ አገልግሎቶችን ያነጋግሩ።

- ☑ ኢንሹራንስ ካልዎት ንብረትዎን ስለመጠበቅ ፣የእቃዎን ዘርዝር ስለማዘጋጀት እና ከእሳት አደጋ መልሰው የሚቋቋሙ ኩባንያዎችን ለማነጋገር ዝርዝር መመሪያዎችን ለማግኘት ወዲያውኑ የኢንሹራንስ ኩባንያዎን ያነጋግሩ። ኢንሹራንስ ከሌለዎት ለእገዛ እና ለእርዳታ የግል ድርጅቶችን ለማነጋገር ይሞክሩ።

- ☑ የመኖሪያ ቦታዎ መልሶ ለመግባት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ከእሳት አደጋ ክፍል ያረጋግጡ። በእሳቱ ምክንያት ለደረሰው ማንኛውም የሕንጻውን መዋቅራዊ ጉዳት በንቃት ይከታተሉ።

- ☑ የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት ከቤቱ ከመውጣታቸው በፊት የፍጆታ መገልገያዎችን (utilities) መጠቀም እንዲቻል ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ወይም እንደተቋረጡ ማረጋገጥ አለባቸው። የፍጆታ መገልገያዎችን (utilities) እራስዎ ለማገናኘት (እንዲሰራ ለማድረግ) **አይሞክሩ**።

- ☑ የተበላሹ ንብረቶችን እና ዕቃዎችን ዝርዝር በመመዝገብ ያስቀምጡ። እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ሳያልቁ የተበላሹ/የወደሙ እቃዎችን እንዳይጥሉ፡፡

- ☑ ጠቃሚ ሰነዶችን እና መዝገቦችን ለማግኘት ይሞክሩ። መረጃ ለማግኘት ማንን ማነጋገር እንዳለብዎት እና ከመተካት ሂደት ጋር በተያያዘ ያለውን መረጃ በዚህ ሰነዶች ውስጥ የቀረበውን ይከተሉ።

- ☑ ቤትዎን ለቀው ከወጡ፣ ማንም ሰው በቤቱ እንደማይኖር ለማሳወቅ የአካባቢውን የፖሊስ መምሪያ ያነጋግሩ።

- ☑ ከእሳት መጥፋት ጋር በተያያዘ ለሚያወጡት ማንኛውም ወጪ ደረሰኞችን በአግባቡ ማስቀመጥ ይጀምሩ። ደረሰኙ በኋላ በኢንሹራንስ ድርጅቱ እና በገቢ ታክስ በሚያሰሩበት ወቅት የጠፉቦትን ለማሳወቅ ሊያስፈልግዎ ይችላሉ፡፡

- ☑ ስለ እሳት አደጋው የቤትዎን የሞርጌጅ ካምፓኒ (mortgage company)ያሳውቁ።

- ☑ ከኪሳራ የሚያገግሙ ሰዎች ልዩ ድጋፎችን በተመለከተ ከሂሳብ ባለሙያ ወይም ከሀገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት (Internal Revenue Service) ያረጋግጡ።